እትም 2
ቁጥር 2

AHRE

2013

# ሰብአዊነት

## የስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ መፅሄት



**ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ ከመተከል እስከ መቀሌ (ክፍል ሁለት)**

ኖህ የሱፍ|ገፅ 2

**HIGHLIGHTING THE TRANSITION AND YOUTH POLITICAL PARTICIPATION IN ETHIOPIA**

Befekadu Dereba | ገፅ 7

**የሥርዓተ-ፆታ ኮታ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ለማረጋገጥ**

ማህሌት አብረሃም|ገፅ 11

**የንፁሀን ጥበቃ በጦርነት ወቅት (ክፍል ሁለት)**

ማህሌት ንጉሴ | ገፅ 14

## አዘጋጆች

**ዋና አዘጋጅ**
**ቃልኪዳን ተስፋዬ**
በኮምፒውተር ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ
በእንግሊዘኛ ቋንቋ እና ስነ-ጽሁፍ የሁለተኛ ዲግሪ
ጸሀፊ፣ ገጣሚ እና የኮሚኒኬሽንና አድቮከሲ ባለሙያ
e-mail- kalkidanzewde4@gmail.com

**የህትመት ዲዛይነር**
**ቤርሳቤህ ሰለሞን**
ከድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ
ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰብአዊ መብቶች ህግ የሁለተኛ ዲግሪ
e-mail- solomonbersabeh19@gmail.com

**አርታኢ**
**ኖህ የሱፍ**
ከወሎ ዩኒቨርሲቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ
ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰብአዊ መብቶች ህግ
የሁለተኛ ዲግሪ ተማሪ
e-mail- noahyesufyimer@gmail.com

**የህትመት አስተባባሪ**
**ማህሌት ንጉሴ**
ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ
e-mail- mahletnegussie12@gmail.com

**በዚህ መጽሄት ውስጥ የተካተቱት ጽሁፎች የጸሀፊዎቹ ሃሳብና አስትያየቶች ሲሆኑ ድርጅታዊ አቋምን አያመላክቱም።**

**Get in touch with us!**
Our official website at https://ahrethio.org
+251 910921294 edenjossy2005@gmail.com
Telegram channel
https://t.me/AHREEthiopia
Facebook
https://www.facebook.com/AHREthio.org

## ርዕስ አንቀጽ

ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጲያ (ስሰመኢ) መንግስታዊ ያልሆነ፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ እና ከፖለቲካ ነፃ የሆነ ለሀገራችን ሰብአዊ መብቶች አያያዝ መሻሻል ጥልቀት ያላቸው የሰብአዊ መብት ምርምሮችን በመስራት በማስረጃ የተደገፉ ምክረ ሀሳቦችን የሚያቀርብ እና በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎችን የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

ስሰመኢ ከተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጪ ድርጅቶች ጋር በትብብር ለተመሳሳይ አላማ በመስራት ያምናል፤ በመሆኑም ከተለያዩ አለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ድርጅቶች ጋር ይሰራል፡፡ በተጨማሪም ለተለያዩ የሀገር ውስጥ ሲቪል ማህበራትና ሌሎች ድርጅቶች ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ ስልጠናዎችን በመስጠት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ስራዎች በተጨማሪ ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጲያ በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ የሚያጠነጥን እና ሰብአዊነት በሚል ርዕስ የሚያሳትመውን መጽሄት ከሚያዚያ ወር 2013 ዓ.ም ጀምሮ ለአንባቢያን እያቀረበ ይገኛል፡፡ መፅሄታችን የተለያዩ በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ግንዛቤን የሚፈጥሩ እንዲሁም በወቅታዊ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ ያተኮሩ ጽሁፎችን የሚይዝ ሲሆን የድርጅታችን ሰራተኞች እንዲሁም ከውጪ ያሉ ጸሀፊዎች ስራዎቻቸውን የሚያቀርቡበት አምድ ነው። አብዛኞቹ በመጽሄቱ ውስጥ የሚታተሙት ጽሁፎች ወቅታዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ ያስገቡ እና አፋጣኝ ትኩረትን የሚሹ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም መፅሄቱ አንባቢያን ሰብአዊ መብቶችን በተመለከት ግንዛቤ የሚያገኙበትን እንዲሁም ጸሀፊዎች ያስተዋሏቸውን ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ለማህበረሰቡ እና ለሚመለከታቸው አካላት የሚያደርሱበትን እድል የሚፈጥር ነው፡፡ በመሆኑም ተደራሽነቱን ታሳቢ በማድረግ በመጽሄቱ የሚካተቱ አብዛኛዎቹ ጽሁፎች በአማረኛ የሚሆኑ ሲሆን በእንግሊዘኛ የተጻፉ ጽሁፎችም የሚካተቱ ይሆናል።

በመሆኑም በዚህ እትም ከባለፈው እትም የቀጠሉ ሁለት ጽሁፎችንና እንዲሁም ሁለት አዳዲስ ጽሁፎች ተካተዋል። በመሆኑም ድንበር አጣሪ ኮሚቴን በተመለከተ፤ አለም አቀፍ የጦርነት ህግን በተመለከተ፤ የወጣቶች ተሳትፎ በምርጫ ወቅት ምን ይመስላል እና የስርአተ ጾታ ኮታ ለሴቶች ተሳትፎ ያለውን ሚና የሚዳስሱ ጽሁፎች ቀርበዋል።

# ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ ከመተከል እስከ መቀሌ - (ክፍል ሁለት)

**ኖህ የሱፍ**

## ገለልተኛ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት አጣሪ ጉባኤ የማቋቋም ተሞክሮዎች

በኢትዮጵያ ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤን በተመለከተ ሁለት የቅርብ ተሞክሮዎች አሉ። ይሁን እንጅ ከነዚህ በፊትም በደርግ ጊዜ 15 አባላት የነበሩት አጣሪ ኮሚቴ ነበር፡፡[1] ይህ አጣሪ ኮሚቴ በንጉሱ ጊዜ የነበሩ ከ150 በላይ የሚደርሱ ከፍተኛ ባለስልጣናት ፈፅመውታል የተባሉ ወንጀሎችን ለማጣራት በደርግ ወታደራዊ መንግስት የተቋቋመ ነው፡፡ ወታደራዊ መንግስቱ ይህንን አጣሪ ኮሚቴ አቋቁሙ የነበረ ቢሆንም የኮሚቴው ሪፖርት ለህዝብ ይፋ አልተደረገም፡፡

ከዚህ በመቀጠል ከሁለቱ የቅርብ ተሞክሮዎች የመጀመሪያው በጋምቤላ ብሄራዊ ክልል በ1996 የተከሰተውን የሰብአዊ መብት ጥሰት ለማጣራት በአዋጅ ቁጥር 398/1996 የተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን ነው። ይህ ኮሚሽን ምንም እንኳን በአዋጅ ቢቋቋምም ሪፖርቱ ለህዝብ ይፋ ያልተደረገ እና ገለልተኛ ያልነበረ በገዢው ፓርቲ ተፅዕኖ ስር የወደቀ ኮሚሽን ነበር። ሁለተኛው የአጣሪ ኮሚሽን ማቋቋም ተሞክሮ ከ1997 ምርጫ በኋላ የተፈፀሙ ከፍተኛ ግድያዎችን ወይም የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለማጣራት በታህሳስ 1998 በአዋጅ ቁ. 478/2005 የተቋቋመው አጣሪ ጉባኤ ነው፡፡[2] ይህ ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ መንግስት ከምርጫ በኋላ የወሰዳቸውን እርምጃዎች ተመጣጣኝነት እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ለማጣራት የተቋቋመ ነው፡፡ አጣሪ ጉባኤው በመንግስት ተፅዕኖ ሲደረግበት የነበረ ሲሆን አብዝሃኞቹ አባላት በያዙት ገለልተኛ አቋም ችግር ደርሶባቸዋል። አጣሪ ጉባኤው በሪፖርቱ መንግስት የወሰዳቸው እርምጃዎች ተመጣጣኝ አለመሆናቸውን ከአስር የኮሚቴው አባላት ስምንቱ ደግፈውት ውሳኔው ተላልፏል። ይህ ሪፖርት ፓርላማው ከአመታዊ መዝጊያ ቀናት በፊት በመበተኑ ሪፖርቱ እንዳይሰማ የተደረገ ሲሆን የአጣሪ ኮሚሽን አባላቱም ያሳለፉትን ውሳኔ እንዲቀይሩ በመንግሥት ጫና እና ማሥፈራሪያ ሲደረግባቸው ነበር። በዚህም የተነሳ የአጣሪ ኮሚሽኑ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና አንድ አባል በምስል የተደገፈ ማሥረጃውን በመያዝ ከሀገር ተሰደዋል።[3] ይህ ይሁን እንጅ መንግስት ሌሎች ገለልተኛ ያልሆኑ ሰዎችን በመምረጥ ውሳኔው ተቀልብሶ መንግስት የወሰዳቸው እርምጃዎች ተመጣጣኝ ናቸው በሚል በመቀየር በጥቅምት 1999 ለፓርላማ እንዲቀርብ ተደርጓል፡ ስለሆነም እነዚህን የሀገር ውስጥ ተሞክሮዎች ከገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን አመሰራረትና አሰራር መርሆች አንፃር ብቁ እና ገለልተኛ ነበሩ ለማለት አያስችልም።

**ለዚህም በዋና ማሳያነት ስንመለከት፡-**

1ኛ አባላቱ ምንም እንኳን የህግ ሙያ እና ልምድ ያላቸው ጥቂት አባላት ቢኖሩም አብዛኞቹ አባላት ከእምነት

[1] David Ottaway, 'From the archive, 24 August 1974: Ethiopia's fallen aristocrats' (The Guardian August 24, 2015) <https://www.theguardian.com/world/2015/aug/24/ethiopia-aristocracy-revolution-civil-war-1974> accessed May 24, 2021.

[2] An Inquiry Commission to investigate the disorder occurred in Addis Ababa and in some parts of the country proclamation No. 478/1998.

[3] ESAT Special Sene 1 victims & inquiry commission June 2012 Ethiopia (ESAT June 2012) <https://www.youtube.com/watch?v=1Gisf3MenFs&t=432s> accessed May 25, 2021.

ተቋማት እና ሌሎች ቦታዎች የተመረጡ በመሆኑ ማጣራቱ በሚፈልገው የሙያ ችሎታ ላይ ግንዛቤ እና ልዩ የምርመራ ብቃት (expertise) የሌላቸው ነበሩ። ይህም የማጣራቱ ሂደት በሚጠይቀው የሙያ ሂደት (የሰብአዊ መብቶች እውቀት) ሳይኖራቸው አባላቶች ድምፅ እንድሰጡ ያደረገ እና የአጣሪ ኮሚሽን መርህን ያልተከተለ ነበር።

2ተኛ የ1997 ምርጫን ተከትሎ የተቋቋመውን ስንመለከት የመንግስት ግልፅ ጣልቃ ገብነት እና የኮሚሽኑ አባላት ገለልተኛ ሆነው ስራቸውን እንዳያከናውኑ የተደረገበት እና ያስተላለፉት ውሳኔ የተቀለበሰበት ነበር።

3ተኛ ጋምቤላ ላይ ለተከሰተው የሰብአዊ መብት ጥሰት የተቋቋመው መርማሪ ኮሚሽን የመንግስት ቁርጠኝነት የሌለበት የነበረ ሲሆን ሪፖርቱም እንዳይወጣ ተደርጓል።

ከእነዚህ ተሞክሮዎች ልምድ መውሰድ እንደሚቻለው ለሚቋቋሙ ኮሚሽኖች መንግስት ቁርጠኛ፣ ገለልተኛ እና የአጣሪ ኮሚሽን ውሳኔዎችን የሚቀበል መሆን እንዳለበት ፤ በሚፈለገው የሙያ ችሎታቸው ላቅ ያሉ አባላትን ማካተት እና የአባላቱን ነፃነት እና ገለልተኝነት ማክበር መቻል እንዳለበት ነው። በመሰረቱ እነዚህ የተቋቋሙ ሁለት ኮሚሽኖች መንግስት ከወሰዳቸው እርምጃዎች እና ከፈፀማቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ጋር በቀጥታ የተገናኙና የመንግሥትን እርምጃዎችን ለማጣራት የተቋቋሙ ናቸው ብለን ልንወስዳቸው እንችላለን። ለዚህም ነው በአባላቱ ላይ የማሥፈራራት፣ የማሳደድ እና ሪፖርቶቻቸው እንዲቀለበሱ እና እንዳይወጡ የተደረጉት። ይህ ይሁን እንጅ መንግስት እራሱ በግልፅ እና በቀጥታ የፈፀማቸውን ጥሰቶች በገለልተኛ አካል እንዲጣሩ አጣሪ ኮሚሽን ማቋቋሙ እንደ አንድ አዎንታዊ እንቅሥቃሴ ሊወሰድ ይችላል።

ከዚህ አንፃር የአሁን ጊዜ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለማጣራት ያለውን ቁርጠኝነት ስንመለከት በመንግሥት በኩል ከ1997 እና 1996 ከተቋቋሙት በተሻለ ቁርጠኝነት አለ ለማለት አያስደፍርም። ይህም ሲባል ለምሳሌ የበፊት ተሞክሮዎችን ስንመለከት ቀጥታ መንግስት የወሰዳቸው እርምጃዎችን መንግስት ደፍሮ ለማጣራት አንድ እርምጃ በመንቀሳቀስ አጣሪ ኮሚሽኖችን አቋቁሟል። ነገር ግን በአሁን ጊዜ የሚፈፀሙት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በአይነት እና ባህሪ ለየት ያሉ አለፍ ሲልም በአብዝሃኛው መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት የሚፈፀሙ ሆነው እያለ ከመንግስት የፖለቲካ ቁርጠኝነት ባለመኖሩ አጣሪ ጉባኤዎችን ማቋቋም አልተቻለም። ይህ ሆኖ እያለ ምንም እንኳን እየተከሰቱ ባሉት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ላይ መንግስት ከተጠያቂነት ማምለጥ የሚችልበት ሁኔታ ባይኖርም ከቅርብ ጊዜ ወድህ እንደ መተከል እና በመሳሰሉት የሀገሪቱ አካባቢዎች ለተከሰቱ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መንግስት ገለልተኛ አጣሪ በማቋቋም ለዜጎች ሰብአዊ መብት መከበር ቁርጠኛ መሆኑን ማሳየት ይገባዋል።

## የገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ አስፈላጊነት ከየት እስከ የት ላለው ጥሰት?

ባለፉት ሶስት አመታት በኢትዩጵያ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታን የማሻሻል አንዳንድ እርምጃዎች ተወስደዋል። ህጎችን በማሻሻል፣ ገለልተኛ ተቋሞችን ለመፍጠር የሚያስችሉ መሰረቶችን በመጣል፣ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ምክክር በማድረግ እና ሌሎች እርምጃዎችን በመውሰድ ጥሩ ምልክቶች ታይተዋል። ለሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በነጻነት የሚንቀሳቀሱበትን ምህዳር በማስፋት እና ለአንዳንድ የአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪ ድርጅቶች ተዘግቶ የቆየውን በር በመክፈት የሚበረታቱ በጎ እርምጃዎች ታይተዋል። ምንም እንኳን እነዚህ በጎ የሚባሉ የለውጥ ምልክቶች ቢታዩም ጎን ለጎን ሀገሪቷ ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ቀውሥ ውስጥ የገባችበት እና ዜጎች ለጅምላ ግድያ፤መፈናቀል፣ በማንነት ላይ ላነጣጠሩ

ጥቃቶች፣ ለጦርነት እና የደረሱበት አለመታወቅ ወይም ታፍኖ መሰወር የተዳረጉበት በርካታ ክስተቶች ተፈጽመዋል። ባለፉት ጥቂት አመታት በሀገራችን የተከሰቱትን ከፍተኛ የሙብት ጥሰቶች እና ያለውን ነባራዊ ሁኔታ እንደሚከተለው በመጠኑ እንመልከት፡፡

## የቡራዩ ብሔር ተኮር ጥቃት ሲታወስ

በሀገራችን ህዝባዊ እምቢተኝነትን ተከትሎ የመጣው ለውጥ ከገጠሙት ሰፊ ተግዳሮቶች አንዱ በበርካታ የሀገሪቱ ክፍሎችች እጅግ አሰቃቂ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት መፈፀም ነው። ከእነዚህ ክስተቶች መካከል በቡራዩ ከመስከረም 03 ቀን 2011 እስከ መስከረም 05 ቀን 2011 የተፈፀመው የዜጎች እልቂት አንዱ ነው። ይህንን የዜጎች እልቂት በጊዜው "መንግሥት በማጣራት ላይ ነው" የሚል መግለጫዎች የተሰጡ ቢሆንም እስካሁን ጉዳዩ የሚገኝበት ሁኔታን በተመለከተ ለህዝብ የተጣራ እና ግልፅ የሆነ መልስ  በመንግስት ደረጃ አልተሰጠም።

ሌሎች የከፉ ጥቃቶች በተከታታይ ሲፈጸሙ በመቆየቱ፤ እንዲሁም የመንግስት እና የሕዝብን ቀልብ የሚስቡ ሌሎች በርካታ እና አዳዲስ ሁኔታዎች ያለሟቋረጥ ይከሰቱ ስለነበር የቡራዩን ጉዳይ ተደባብሶ እንዲቀር ምክንያት ሆኗል። አጥፊዎች ተብለው እና ተጠርጥረው የተያዙ ሰዎች ስለመኖራቸው በወቅቱ ለሕዝብ ይፋ የተደረገ ቢሆንም የፍትህ ሂደቱ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ፣ የተቀጡም ሰዎች ካሉ ስለ ፍርድ ሂደቱ እና ምን እንደተቀጡ ለሕዝብ የተገለጸ ነገር የለም። ይህም 'እውነት' በየቀኑ በሚከሰቱ ሁነቶች ተሸፍና እንድትቀር አድርጓል። ነገር ግን መንግስት እነዚህን ጥሰቶች በአግባቡ የማጣራት ፣ የመመርመር እና ለተጎጂ ዎች ፍትህ የመስጠት ህጋዊ ግደታ አለበት። ስለሆነም የተፈፀሙት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እውነታውን ለህዝብ በጊዜ እና በተአማኒነት ለማድረስ ተጎጅዎችም እውነታውን የማወቅ እና ፍትህ የማግኘት መብታቸውን ለማስከበር ነፃ እና ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ማቋቋም አሥፈላጊ ነው።

## መተከል

ባለፉት ሶስት አመታት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በመተከል ዞን እና በሌሎች የክልሉ አካባቢዎች በተደጋጋሚ የተከሰቱት የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ብዙዎችን ለህልፈት የዳረጉ ከመሆናቸውም በላይ በመቶ ሺ የሚቆጠሩትን ከቤት ንብረታቸው ያፈናቀሉ ክስተቶች ናቸው። በክልሉ ውስጥ ያለውን አሳሳቢ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ኢሰመጉ) "መቆምያ ያጣው የንፁሃን እልቂት"[4] በሚል ርዕስ ባወጣው ጠቅለል ያለ ዘገባ  በክልሉ ከነሃሴ 2012 እስከ ታህሳስ 2013 ባሉት 5 ወራት ውስጥ ብቻ በተሰነዘሩ ጥቃቶች ከ500 በላይ ሰዎች ሲገደሉ ከ100 ሺ በላይ ሰዎች መፈናቀላቸውን ገልጿል። ይህ የግድያ እና የማፈናቀል እርምጃ በተመለከተ ከመንግስት በተደጋጋሚ እንደሚገለጸው ድርጊቱን የሚፈጽሙት በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ ሽማቂ ኃይሎች መሆኑን ነው። ጥቃቶቹን ተከትሎም መንግስት በእነዚህ አማጺ ኃይሎች ላይ ተመጣጣኝ እርምጃ እየወሰደ መሆኑን ሲገልጽ ቆይቷል። ይሁን እና የመንግስት እርምጃ ጥቃቱ ለማስቆም ባለመቻሉ በርካታ ንፁሃንን ከተደጋጋሚ ጥቃት ሊታደጋቸው ሳይችል ቆይቷል።

ይህ ችግር ለረዥም ጊዜ እልባት ሊያገኝ ያልቻለበትን ምክንያቶች በተመለከተ ብዙ መላምቶች እና ግምቶች ቢኖሩም በዋነኝነት ግን እንደ መንስኤ የሚጠቀሰው እና በመንግሥትም ጭምር እንደ ዋነኛ ችግር የተጠቀሰው

[4] Ethiopian Human Rights Council, 'መቆሚያ ያጣው በመተከል ያሉ ሰዎች እልቂት!' <https://ehrco.org/2021/01/> accessed May 25, 2021.

በክልሉ ውስጥ በተለያየ የእርከን ደረጃ ላይ የሚገኙ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ እልቂቱ እንዲከሰት እና እንዲባባስ የሚደግፉ እና የሚያበረታቱ የመንግስት አመራሮች መኖራቸው ነው።[5] ነገር ግን መንግስት ይህንን ጉዳይ ከማመን እና ለተጎጅዎች የእለት ፍጆታ ድጋፍ ከመስጠት በዘለለ ለደረሰባቸው የሰብአዊ መብት ጥሰት ፍትህ እና ለደረሰባቸውም በገንዘብ የሚተመን ጉዳት ተመጣጣኝ የሚሆን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ አልተቻለም። በመሆኑም በክልሉ ውስጥ በቅርብ ጊዜ በደረሱት ጥቃቶች ምን ያህል ሰዎች እንደተገደሉ፣ ምን ያህል ሰው እንደተፈናቀለ፣ ምን ያህል የንብረት ውድመት እንደደረሰ እና ምን ያህልም ሰው ቀላል እና ከባድ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑን በአግባቡ ሰንዶ ሪፖርት የሚያቀርብ፣ ተጎጅዎችን መልሶ ማቋቋም ስለሚቻልበት ሁኔታ በቂ ጥናት አድርጎ ሃሳብ የሚያቀርብ፣ ለተጎጂዎች ተመጣጣኝ የሆነ የጉዳት ካሳ እንዲሰጥ እና አጥፊዎችም ለፍርድ ቀርበው ተጠያቂ የሚሆኑበትን መንገድ የሚያመቻች ገለልተኛ የሆነ አጣሪ ኮሚሽን ማቋቋም አስፈላጊና ጊዜ የማይሰጠው እንዲሁም ዘላቂ መፍትሄ ሊያመጣ የሚችል መንገድ ነው።

### በትግራይ ክልል ያሉ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ጉዳይ

በቅርቡ መንግስት የህግ ማስከበር እርምጃ ነው ባለው በሰሜን ኢትዮጵያ ትግራይ በተካሄደ ኦፐሬሽን በርካታ ሰዎች ለተለያዩ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ተዳርገዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘም በትግራይ ክልል የሚኖሩ ዜጎች እስካሁንም ድረስ በቀጠለ ሁኔታ በአንዳንድ አካባቢዎች የመብራት፣ የኢንተርኔት እንዲሁም የህክምና እና ሌሎች አገልግሎቶችን ማግኘት ያልቻሉ መሆናቸው በተለያዩ ዘገባዎች ሲገለጽ ቆይቷል። ምንም እንኳን መንግስት በጦርነቱ ለደረሱ አስከፊ ክስተቶች እና ጉዳቶች የሚያደርገው ድጋፍ የሚበረታታ ቢሆንም ተጠያቂነትን ከማሰፈን አንፃር እና በክልሉ ያለውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ በየጊዜው ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በክልሉ ያለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ሴቶች ለአሥገድዶ መድፈር ፣ በርካታ ዜጎች ደግሞ ለዝርፊያ እና ግድያ የተዳረጉበት መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። ስለሆነም መንግስት የተፈፀሙትን ጥሰቶች በማንና እንዴት እንደተፈፀሙ፤ የጉዳቱን መጠን እንድሁም ተጎጅዎች በገለልተኛ አካል የተጣራ እውነታን እንድያውቁ እና ተገቢውን ካሳ እንድያገኙ ለማስቻል ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ማቋቋም ያስፈልጋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽነር ጋር ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ የሚደረገው የጣምራ ምርመራና ማጣራት የሚበረታታ ነው፡፡

በሌላ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ደግሞ መንግስት በወለጋ-ጉሊሶ፣ በአጣየ እና አካባቢው እንድሁም በማይካድራ የተፈፀሙትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶች በተለይም ከ700 በላይ የሰው ህይወት የጠፋበትን የማይካድራ ክስተት በትኩረት እንዲጣራ እና ይህንን አለም አቀፍ ወንጀል የፈፀሙ እንድታወቁ ፣ ለፍርድ እንድቀርቡ እና ተጎጅዎች እውነታውን የማወቅ እንድሁም መልሶ የመቋቋም እድል እንድያገኙ ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ በማቋቋም አሥፈላጊውን እንቅሥቃሴ ሊያደርግ ይገባል።

### የማጠቃለያ ሃሳቦች

መንግስት ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ሲያቋቁም ልብ ሊላቸው የሚገቡ መርሆች አሉ፡፡ ከላይ በተጠቀሱት አስከፊ የመብት ጥሰቶች ዙሪያ ገለልተኛ አካል እንዲያጣራ መንግስት በመጀመሪያ ደረጃ ቁርጠኛ የፖለቲካ ውሳኔ

[5] Negasa Desalegn, 'በዞኑ የክልል ም/ ቤት አባላትን ጨምሮ 9 አመራሮች በቁጥጥር ስር ዉለዋል' (DW 04/01/2021) <https://www.dw.com/am/ መተከል-ዞን-በኮማንድ-ፖስት-እንዲጠበቅ-ተወሰነ/a-55041693> accessed May 25, 2021.

መኖር ማለትም የሚወጡ የአጣሪ ኮሚሽን ሪፖርቶችን ለህዝብ ይፋ የማድረግ እና ውሳኔዎችን መሰረት በማድረግ ተጠያቂነትን የማስፈን ሂደት እና ግንዛቤ መኖር ሲሆን፣ ሁለተኛ: ለአጣሪ ኮሚሽኑ በቂ ሀብት መልቀቅን ይመለከታል። ሶስተኛ: ነፃ ፣ገለልተኛ እና ብቁ ባለሙያዎችን እንድካተቱ ማድረግ እንድሁም የሚቋቋመው ኮሚሽን በመርህም በተግባርም ነፃ እና ገለልተኛ እንድሆን ማድረግ ነው። በመጨረሻ አጣሪ ኮሚሽኑን እንደ መንግስታዊ ተጠያቂነትን የማምለጫ መንገድ አለመጠቀም እና ሌሎችም ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በሀገራችን የተከሰቱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን አይነት፣ መጠንና በሰብአዊ መብቶች ጥሰት የተሳተፉትን ለማወቅ እንድሁም የዜጎችን ሰብአዊ መብት መከበር ለማረጋገጥ ገለልተኛ የሰብአዊ መብት አጣሪ ጉባኤ ማቋቋም ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር ግን፤ ገለልተኛ አጣሪ ጉባኤ በተወሰኑ ቦታዎች ለተከሰቱ ጥሰቶች ወይስ እንደሃገር የተከሰቱትን የሰብአዊ መብቶች ቀውስ በአጠቃላይ ለማጣራት የሚለው ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

# Highlighting the Transition and Youth political Participation in Ethiopia

**Befekadu Dereba**

**Abstract**

*Youths are the milestone for every emerging democratization process in the world. For the current political juncture, Ethiopia's youth have given their unreturned souls to voice the people's mutual concerns and bring about the transition. However, their meaningful participation and needs have not been prioritized, and they have been given little room to participate in formal decision-making. As a result, most young people are skeptical of the transition and pessimistic about the country's overall social, economic, and political status. In this short article, a political representation of the youth, and their participation in the post-transition period will be discussed.*

## Nature of the Current Political Transition of Ethiopia

At the outset, there are three transitional paradigms.[6] The first is a replacement or overthrow. In this model, political transition is triggered when armed opposition groups overthrew the incumbent government and hold the political power through war, and violence. The second is transformation or reform; it is when the transition is promoted by the incumbent government itself. It is a kind of inner-out political change. Lastly, Tran's placement or compromise transition emerges from both existing government and opposition groups.[7] There is a political bargain from both sides.[8]

Ethiopia's present political change does not appear to be a pure transformation model; rather, it appears to be a hybrid of both transformation and Tran's placement models.[9] It can be argued that some of the present reforms are being made to quell public outrage and maintain the status quo in the government.[10] Of course, the incumbent government has made efforts to organize different dialogue and negotiation forums to discuss with some political parties.[11] However, these discussions and negotiations were not fruitful as they were expected due to

[6] Seely, J. *The Legacies of Transition Government in Africa: The Cases of Benin and Togo. Palgrave Macmillan*, 2009, pp.12.
[7] Ibid.
[8]Giuseppe, P. *Democracies: An Essay on Democratic Transitions. Berkeley*: University of California Press, 1990.
[9] Mulualem Daba Tola, 'Qeerroo Fi Qarree': The Engine of Current Transition In Ethiopia Politics, International Journal of Scientific and Research Publications, Volume 9, Issue 5, May 2019, www.ijsrp.org .
[10] Ibid.
[11] Mukerrem M. OP: ED: *Ethiopia in Transition Is Facing Critical Challenges.* Addis Standard. Retrieved from http://addisstandard.com, 2018, pp 5.

the competitive nature of negotiation than a collaborative one among opposition parties and the existing government.[12] Therefore, the current political transition of Ethiopia inconclusive, and as Mukerrem, stated it seems a "hybrid" or "grey zone, which is not trusted by most youths.[13]

**Who are the youth?**

Youth can best be described as a phase of transition from childhood dependence to adulthood's independence. Age-based categorizations are often used to frame policy interventions in areas such as education, health, and criminal justice in different countries. The United Nations defines those between the ages of 15 and 24 as a youth.[14] The African Youth Charter on the other hand defines youth as every person between the ages of 15 and 35 years.[15] The Council of European Recommendation on the Participation of Children and Young People counts youth as below the age of 18.[16] The Ethiopian National Youth Policy (NYP) is one of Ethiopia's most significant youth-specific state documents and goes on to define youth as people between 15 and 29 years.[17] Today in Ethiopia, young people are apprehensive at political participation, unlike their elders. Some of the factors that affect youth participation in political processes include the lack of political knowledge and adequate education, less political interest, and the economic factor.[18] Youth have limited social and political power while the elder people tend to dominate decision-making at all levels.

**Legal & policy framework for youth political participation**

Basic human rights, such as the ability to fully engage in a country's political and electoral processes, are recognized in a large body of international and regional legal instruments, such as the Universal Declaration of Human Rights (UDHR, 1948)[19] and ICCPR. Over the last decade, the international community has re-affirmed its commitment to youth participation in several resolutions, charters, and action plans, such as the African Youth Charter.[20] Although FDRE Constitution does not contain an explicit article guaranteeing the political participation of the youth it contains provisions under Art 38 as youth can participate in the election on the attainment of 18 years. The reformed electoral law of Ethiopia is yet silent about youth political participation. The participation of youth in Ethiopia is more addressed through different

[12] Supra note, 4.

[13] Ibid.

[14] Secretary-General's Report to the General Assembly, A/36/215, 1981.

[15] African Union, African Youth Charter, 2006, www.un.org/en/africa/osaa/pdf/au/african_youth_charter_2006.pdf.

[16] The council of European Recommendation, Adopted by the committee of ministers on 28 March 2012 at the1 138th meeting of the minister's deputies

[17] Ethiopian National Youth Policy (NYP), 2004 cited in Supra note 6.

[18] Getachew Mijana Sabu. Factors That Affect Youth Political Participation in Ethiopia: Its Impacts on the Democratization Process, Journal of Political Science and International Relations. Vol. 3, No. 3, 2020, pp. 61-69.

[19] The Universal Declaration of Human Rights has codified everyone's "right to take part in the government of his country, directly or through freely chosen representatives" (Article 21), www.un.org/en/universal-declaration-human-rights/

[20] Supra note at 6.

youth policy frameworks. Hence, the first youth policy is the NYP. The objectives of the policy include: to bring about the active participation of youth in socioeconomic, political, and cultural activities.

**Pathways for youth Political participation**

The recent Ethiopian demonstration towards the need for democracy, equality, justice, and human rights are fueled by young generations and still, they are to demand a voice in the decisions that affect their lives. The first pathway is their involvement in institutional politics**:** Although young people between the ages of 15 and 24 constitute about one-fifth of the world's population[21] their participation and influence informal politics remain limited. Ethiopia is not an exception to this. Empirical research shows that in contemporary Ethiopia, young people are not meaningfully participating in the formal political system.[22] Recent years have seen the power of youth mobilization in Ethiopia in which political parties have been able to mobilize youth for both constructive and destructive political agendas. However, their meaningful participation and their needs have not been yet prioritized and they have been offered little space in the 2021 election held by Ethiopia. The other way of their participation is their involvement in Protest activities**,** when frustrations have escalated youth groups have been turning to civil disobedience and violence. One of the recent pathways for youth political participation is the youth protest across the country particularly in Oromia which marks a change in Ethiopia's political landscape. This protest is not ending up yet and it is the big question of whether the transition has achieved its goal and answered youth's quests. Therefore Youth sector policy formulation requires the active engagement of young people. The third and last resort that youth will use is an armed struggle**.** It has been a pathway for youth political participation in Ethiopia since the Student Movement. Nowadays a more youth inclusive armed groups of OLA or as the government called them "OLF Shane"[23]and TPLF is fighting with the government of Ethiopia on different fronts of the country causing th deaths of many everywhere.

**Conclusion and Recommendation**

The peaceful end of 2021's election is expected to lay the foundation for genuine democracy and correcting political culture that has resulted in disrespect and hostility among Ethiopia's ethnic groups. Moreover, the new government that comes to power should ensure a formal political participation of the youth. It is expected to amend electoral and other laws to bring the equal participation of youth through reserved seats or Legal candidate quotas within the political parties to ensure that a minimum of young candidates is represented in the formal political system. The scarification of youth to advance a toxic political goal should be

[21] UN-DESA, 'Youth, Political Participation and Decision-Making', www.un.org/esa/socdev/documents/youth/fact-sheets/youth-political-participation.pdf.

[22] Supra note 13.

[23] These groups are labeled as terrorists by the Ethiopian parliament, see Prevention and Suppression of Terrorism Crimes Proclamation No. 1176/2020 cited at https://www.thereporterethiopia.com/article/it-high-time-olf-shane-be-proscribed-terrorist-organization.

stopped. Because democracy is a multi-faceted process, accepting the result of the election while also encouraging debate to build a shared vision is well worth the effort. We are currently experiencing some of the most serious human rights violations in our country, and we urgently want healing, meaningful participation, national discourse, and a shared understanding among all major parties to stop the atrocities. The youth's active role in closing this loophole is undeniable. The administration should pay special attention to youth to prevent them from participating in destructive protests and armed resistance which dejected the democratic process.

# የሥርዓተ-ፆታ ኮታ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ለማረጋገጥ

**ማህሌት አብረሃም**

የሥርዓተ-ፆታ ኮታ ከመደበኛ የፖለቲካ መድረክ የሴቶች ታሪካዊ መገለልን ለማስተካከል እንደ ዓለም አቀፍ ፈጣን ስትራቴጂ ብቅ ብሏል፡፡ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የመጨረሻ አጋማሽ ላይ ብዙ አገራት የሥርዓተ-ፆታ ጥያቄዎችን በፈቃደኝነት ወይም በህግ/በአስገዳጂነት ተግባራዊ እያደረጉ ይገኛሉ። የሥርዓተ-ፆታ ኮታ ማስቀመጥ በተመለከተ የተለያዩ ክርክሮች ይቀርባሉ።በፖለቲካና ምርጫ ሂደት ተሳትፎ የሚስተዋሉትን የስርአተ ጾታ ልዩነቶችን በተለይ ደሞ የሴቶችን አነስተኛ ተሳትፎን ለማሻሻል የሚያስችሉ በጊዜያዊነት ከሚወሰዱ የድጋፍ እርምጃዎች አንዱ በምርጫ ሂደት የኮታ ተግባራዊነት ነው፡፡

በሴቶች ላይ የሚደርሱ ሁሉንም አይነት መድሎዎች ለመቀነስ የጸደቀዉ ቃል-ኪዳን ስምምነት (CEDAW)[24] በአንቀጽ 4 እና 7 እንደደነገገዉ እንዲሁም የአፍሪካ የሴቶች ፕሮቶኮል (ማፑቶ ፕሮቶኮል) አንቀጽ 9 በግልጽ እንዳተተዉ የሴቶችን እኩል የፖለቲካና የምርጫ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ያስችል ዘንድ በጊዜያዊነት የሚወሰዱ የድጋፍ እርምጃዎች ለምሳሌ ኮታ ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማሉ።[25]

የተለያዩ ሪፖርቶች እንደሚያመለክቱት የሥርዓተ-ፆታ ኮታዎች በዓለም ዙሪያ አማካይ ውክልና እንዲጨምር ማድረጉን ያስቀምጣሉ። ሴቶች በፓርላማ ውስጥ ከ ሃያ ሶስቱ ሀገሮች ውስጥ አስራ ስምንቱ ቢያንስ 30% ውክልና ያላቸው ሴቶች በብሔራዊ ፓርላማዎች አንድ ዓይነት የሥርዓተ-ፆታ ኮታ በሕግ ወይም ተግባራዊ አድርገዋል። በተጨማሪም በአማካይ በ2019 የሥርዓተ-ፆታ ኮታዎችን በተጠቀሙባቸው አገሮች ውስጥ 21% የፓርላማ አባላት ሴቶች ሲሆኑ 13% እንደዚህ ዓይነት እርምጃዎች ባልነበሩባቸው አገሮች ውስጥ ነው፡፡[26]

ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸዉ አለም አቀፋዊና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ሰነዶች ዉስጥ እዉቅና ያገኘዉ የኮታ ተግባራዊነት ዋነኛ አላማዉ ሴቶች ከወንዶች እኩል በፖለቲካና ምርጫ ሂደት እንዳይሳተፉ የሚያደርጋቸዉ በርካታ እንቅፋቶች ያሉ መሆናቸዉና፤ እነኚህ እንቅፋቶች በእኩልነት የሚተገበሩ ህጎች በመደንገጋቸዉ ብቻ በፖለቲካና ምርጫ ሂደት የስርአት ጾታ እኩልነትን ማረጋገጥ እንደማይቻል በመገንዘብ ነዉ፡፡ በተጨማሪም በሴቶች ላይ የሚደርሱ ሁሉንም አይነት መድሎዎች ለመቀነስ በጸደቀዉ ቃል-ኪዳን ስምምነት (CEDAW) ዉስጥ የተዘረዘሩ መብቶችና ግዴታዎች መፈጸማቸዉን የሚከታተለዉ ኮሚቴ በተለያዩ ጊዜያት ባወጣዉ ጠቅላላ መግለጫዎቹም ጭምር ሴቶችን በቀደሙ ታሪኮች፣ አስተሳሰቦችና አሰራሮች የተነሳ የደረሰባቸዉን መድሎዎች ለማረምና ለማስተካከል ይረዳ ዘንድ በተጨማሪ የድጋፍ

[24] UN General Assembly, *Convention on the Elimination of All Forms of Discrimination Against Women*, 18 December 1979, United Nations, Treaty Series, vol. 1249, Article4&7

[25] Protocol to the African Charter on Human and People's Rights on the Rights of Women in Africa, (adopted on 28 March 2003 and entered to force 11 July 2003) Article 4, 5 & 9

[26] Abdul Latif Jameel Poverty Action Lab (J-Pal). (2018) Improving women's representation in politics through gender quotas https://www.povertyactionlab.org/policy-insight/improvingwomens-representation-politics-through-gender-quotas

[5] United Nations, *Beijing Declaration and Platform of Action, adopted at the Fourth World Conference on Women*, 27 October 1995 Para 185

እርምጃዎች ተጠቃሚ መሆን እንዳለባቸዉ አጽንኖት ይሰጣል፡፡ ኮሚቴዉ ባለፉት ዘመናት የደረሱትን መድሎዎች ለማረም እኩልነትን የሚያረጋግጡ ህጎች ብቻ ማዉጣቱ በቂ እንዳልሆነም በተደጋጋሚ አስገንዝቧል፡፡ በተመሳሳይ የቤጂንግ መግለጫ[27] የሴቶች እኩልነት ይረጋገጥ ዘንድ ተጫማሪ ድጋፎች ማድረግን አስፈላጊነት ጠቁሟል፡፡

በዚህ መሰረት ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸዉ የደረሰባቸዉን የታሪክ መድሎ ከግምት ዉስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸዉ በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸዉ፡፡ በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግስትና በግል ተቋሞች ዉስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት መሆኑን የኢትዮጲያ ህገ መንግስት አንቀጽ 35 ይደነግጋል፡፡

ከብዙ የአፍሪካና ሌሎች ሀገራት ተሞክሮ መረዳት እንደሚቻለዉ፣ በፖለቲካዉ መስክ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ከሚያስችሉ ቁልፍ እርምጃዎች አንዱ የኮታ ተግባራዊነት ነዉ፡፡ የኮታ ተግባራዊነትን በሚመለከት ምንም እንኳን በ1995 ህገ መንግስት በግልጽ ባይካተትም፤ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸዉ የአለም አቀፍና አህጉራዊ ሰነዶች እንዲሁም የህገ መንግስቱ አንቀጽ 35(3) የኮታ አሰራር እዉቅና ተሰጥቶታል፡፡

በአለምአቀፍ ደረጃ ሶስት አይነት የኮታ አተገባበር ሞዴሎች እንዳሉ ይታመናል፡፡[28] አንደኛዉ ሞዴል ሴቶች ሊኖራቸዉ የሚገባዉን የፓርላማ መቀመጫ ቁጥር የሚወስን ህግ/መመሪያ መቅረጽ ሲሆን (ይሄ አሰራር ቻይና፣ ሞሮኮ፣ ፓኪስታንና ዝምባቡዌ ባሉ ሀገራት ተተግብሯል)። ሁለተኛዉ ሞዴል የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊኖራቸዉ የሚገባዉ የሴት እጩዎችን ቁጥር በግልጽ የሚደነግግ ህግ ሲሆን ይህ ሞዴል በብዙ ሀገራት ተቀባይነት ያገኘ ሲሆን እንደ ቺሊ፣ስፔን፣ዩክሬንና ቡርኪናፋሶ ያሉ ሀገራት ተግባራዊ አድርገዉታል፡፡ [29]ሶስተኛዉ ሞዴል የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደየ አስፈላጊነቱ እያዩ የሴት እጩዎችን ቁጥር መወሰን የሚችሉበት አሰራር ነዉ፡፡ ይህ ሞዴል በኢትዮጵያ፣ደቡብ አፍሪካና ሞዛምቢክ ባሉት ሀገራት ተቀባይነት አግኝቷል[30]፡ ፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት የሥርዓተ-ፆታ ኮታ የሴቶች መገለልን ለማቃለል እና በመደበኛ የፖለቲካ መዋቅር ውስጥ መሳተፋቸውን ለማረጋገጥ ውጤታማ መሣሪያ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡[31] ሆኖም ወሳኝ ጥያቄው በፖለቲካ መዋቅሮች ውስጥ የሴቶች መገኘት በፖለቲካ ውስጥ የሥርዓተ-ፆታ ጉዳዮችን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲዳረስ ያደረገው ምን ያህል ነው? የሚለው ነው፡፡

የሥርዓተ-ፆታ ኮታዎች የሚሠሩት መዋቅራዊ እና ስልታዊ በሆኑ የሥርዓተ-ፆታ ልዩነቶች ሁኔታ ውስጥ ነው፡ ለሴቶች የፖለቲካ መነጠል መዋቅራዊ ችግሮች መፍትሔ ሳያገኙ ፣ የሥርዓተ-ፆታ ኮታ ማካተት ውጤታማ ውክልና

27

28 Mona Lena Krook & Pär Zetterberg "Introduction: Gender Quotas And Women's Representation—New Directions In Research", Representation,2019, Vol 50:3, 289

29 International Institute for Democracy and Electoral Assistance (International IDEA) GENDER QUOTAS DATABASE, available at https://www.idea.int/data-tools/data/gender-quotas/quotas#different accessed on June 20,2021

30 Ibid

31 Sachet, Teresa. 2008. "Beyond Numbers". International Feminist Journal of Politics, 10, no 3, September, 369-386. See also Krook, Mona Lena. 2008. "Quota Laws for Women in Politics: Implications for Feminist Practice." Social Politics 15, no 3, 345-368

አያስገኝም፡፡ ሴቶችን ከህዝብ የፖለቲካ አካባቢ ማግለልን ለማስቀረት ኮታ አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ሴቶችን ለማጎልበት ባለ ብዙ ገጽታ ስትራቴጂ መቅረፅ ተገቢ ነው፡ ፡ ለዚህም ከፖለቲካ ተሳትፎ ጋር ተያይዞ በህዝብ ውስጥ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሀብቶችን እንደገና ማሰራጨት ያስፈልጋል፡፡ ሲቪል እና ኢኮኖሚያዊ መብቶች የሌላቸው ሴቶች የፖለቲካ መብቶቻቸውን ሙሉ በሙሉ ለመጠቀም አያስችላቸውም። ስለሆነም የሥርዓተ-ፆታ ኮታዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ካለው ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብር ጋር መገናኘት አለባቸው፡፡

ሴቶች በክፍል ፣ በብሄር ፣ በሃይማኖት እና በገጠር / በከተማ አስተዳደግ መስመር የተከፋፈሉ ናቸው። በፖለቲካ ውስጥ ያለው የሥርዓተ-ፆታ ልዩነት ብዙ ሴቶችን ወደ ስርዓቱ በማምጣት ብቻ ሊቀለበስ አይችልም፡፡ እንዲሁም ደጋፊ ስልቶች ካልተቀመጡ እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲሠራ የሚያስችል አካባቢ ካልተፈጠረ በስተቀር በፖሊሲ ሊፈታ የማይችል ነው፡፡ ይህ የኮታ አሠራሮች ተፈጥሮ እና ሂደት በአዎንታዊ እርምጃ (Affirmative Action Measures) መደገፍ አለበት፡፡ የኮታ አሠራር ቀጥተኛ ኃይል የሚሰጥ እና ሴቶች በምርጫ ክልላቸው የሚበቁበት መሆን አለበት፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የፖለቲካ ምህዳሩ የሴቶችን የፖለቲካ ተሳትፎ ለማጎልበት በፖለቲካ ውስጥ በኮታ ሲገቡ የሕዝብ እና የግል (Public and Private Life) ክፍፍልን ማለፍ እንዲችሉ መሆን አለበት። ሴቶች ባላቸው የተሳሳተ የማህበራዊ የስራ ክፍፍል ሚና ምክንያት ማለትም እንደ እናቶች እና ሚስቶች በቤት ውስጥ ሀላፊነቶች ስለሚያዙ በፖለቲካ ውስጥ ለመሳተፍ እና ለመወዳደር ወደኋላ ያስቀራቸዋል፡፡[32]

ስለዚህም የትምህርት ፣ የጤና እና የሥራ ዕድል በቀጥታ በፖለቲካ እና በልማት ውስጥ ለራሳቸው ቦታ ለመፍጠር ከሴቶች ችሎታ ጋር በቀጥታ የተቆራኘ ስለሆኑ እነዚህ ላይ መስራት ያስፈልጋል፡፡ የሴቶች የፖለቲካ መብታቸው ንቃተ-ህሊና ለሴቶች ሌላ ወሳኝ አካል በመሆኑ የለውጥ ማህበረሰቦችን በመገንባት የፖለቲካ ንቃተ-ህሊና ፖለቲካን እና ልማት ለመቀየር መስራት አለበት። ጠንካራ የሴቶች እንቅስቃሴ እና ሲቪል ማህበረሰብ በሴቶች ዘንድ በፖለቲካ እና በልማት አቅጣጫ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል አካባቢን የማስቻል ሁኔታ ስላለው ከስርአተ-ጾታ ኮታ በተጨማሪም እነዚህ ጉዳዮች ላይ መስራት ያስፈልጋል፡፡

[32] Dejene Mamo Bekana (2020) *Policies of Gender Equality in Ethiopia: The Transformative Perspective*, International Journal of Public Administration, 43:4, 312-325, DOI: 10.1080/01900692.2019.1628060

# የንፁሀን ጥበቃ በጦርነት ወቅት

# (ክፍል 2)

## አለም አቀፋዊ የሰብአዊ መብት እና የሰብአዊነት የህግ ማእቀፎች ትግበራ በትግራይ ጦርነት

ማህሌት ንጉሴ

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት እና በቀድሞው የትግራይ ክልል መንግስት ግጭት እንደ አሁኑ ወደ ጦርነት ከማምራቱ በፊት የውስጥ ለውስጥ አለመግባባቶች የነበሩበት በተለይም የፌደራል መንግስት በ COVID-19 ምክንያት ምርጫውን ማራዘሙን ይፋ ማድረጉን ተከትሎ የትግራይ ክልል አስተዳደር የፌደራሉን መንግስት ትእዛዝ በመጣስ የራሱን ምርጫ ካካሄደ በኃላ ይበልጥ የተጋጋለና በመጨረሻም ወደ ጦርነት ያመራ ጉዳይ ነው፡፡

ህዝበ ወያኔ ሐርነት ትግራይ (ህወሐት) በፌደራል መንግስቱ እንዲሁም በህገመንግስቱ አንቀጽ 54 መሰረት ፖሊስ እንዲሁም ሚሊሻን የማስተዳደር መብቱን ያለአግባብ በመጠቀም በሀገር መከላከያ ሰራዊት ላይ ጥቃት ፈጽሟል፡፡ ይህንን ተከትሎ በኢፌድሪ ጠቅላይ ሚንስትር ዶ/ር አብይ አህመድ ትእዛዝ የመከላከያ ሰራዊት ፤ የአማራ ክልል ልዩ ሀይል እንዲሁም የአማራ ክልል ሚሊሻ ወደ ትግራይ ክልል በመዝመት ህግ የማስከበር ስራዎችን ሰርተዋል፡፡

በክፍል አንድ እንደተገለጸው ጦርነቶች አለም አቀፋዊ የትጥቅ ትግል *(International Armed Conflict)* ወይም አለም አቀፋዊ ያልሆነ ሀገራዊ ወይም ውስጣዊ (*Non-international Armed Conflict)* ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ ሁኔታ መለስ ብለን ይሄን ሁኔታ ስናጤን የኤርትራ ጣልቃ ገብነትንና የጦርነቱን አይነት በተመለከተ Human rights watch ባወጣው ሪፖርት መሰረት በኢትዮጵያ መንግስት እና በህወሀት መካከል እየተደረገ ያለው ውጊያ ምንም እንኳን የኤርትራ ጣልቃ ገብነት ቢኖረውም እንደ ውስጣዊ የትጥቅ ትግል መቆጠር እንዳለበት ያስረዳል፡፡[33] ምክንያቱም ጦርነቱ በአንድ ሉአላዊ ሀገር እና በሌላ የተደራጀ ቡድን እንጂ በሁለት ሉአላዊ ሀገራት መካከል የተደረገ ባለመሆኑ ነው፡፡[34]

### በንጹሃን ላይ የተፈጸሙ የመብት ጥሰቶች

በክፍል አንድ ተዋጊ ወገኖች ማን ናቸው፣ ንጹሀንስ፣ ለንጹሀን የሚሰጥ ጥበቃ ምንድን ነው ለንጹሃን ንብረቶችስ የሚለውን ከአለም አቀፍ የህግ ድንጋጌዎች ጀምሮ ወደ ሀገራችን በመሄድ በተዋረድ አይተናል፡፡ በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ህጎች ምን ያህል ትግበራ ላይ ውለዋል ንጹሃንስ ምን ያህል መብታቸው ተከብሯል የሚለውን ከትግራይ ክልል ሁኔታ ጋር በማመሳከር እናያለን፡፡

በጦርነት ወቅት ተዋጊ ወገኖች እኩል ግዴታ እንዳለባቸውና በእኩል ሁኔታ የሰብአዊ መብትን እና የሰብአዊነት ህጎችን ማክበር እንዳለባቸው ይህ ካልሆነ ግን ለተጠያቂነት እንደሚጋለጡ እሙን ነው፡፡ በትግራይ

[33] Human Rights Watch ‘Q&A: conflict in Ethiopia and international law’, November 25, 2020 , 12:25 pm, <https://www.hrw.org/news/2020/11/25/qa-conflict-ethiopia-and-international-law> accessed March 20,2021.

[34] Ibid

ጦርነት ወቅት በተለያዩ አካላት የወጡ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በፌደራል መንግስት ፣ በኤርትራ ወታደሮች እንዲሁም በህወሀት ወገን የተሰተዋሉ ከፍተኛ የሙብት ጥሰቶች አሉ፡፡ ከህወሀት ቡድን ብንጀምር በጦርነቱ ወቅት በማይካድራ በዳንንላት መንደር ውስጥ ሳምሪ በተባለ የጥፋት ቡድን በመጠቀም ከ600 በላይ በሚሆኑ ንጹሀን ኢትዮጵያውያን ላይ አሰቃቂ ግድያ መፈጸሙን የሰብአዊ መብት ኮሚሽን በዳሰሳ ሪፖርት አረጋግጧል[35]፡፡ ከዚህ በዘለለ የህወሃት ቡድን በጦርነቱ ወቅት አለም አቀፉን የህግ ድንጋጌዎችን በመጣስ እድሜያቸው ለውግያ ያልደረሱ ህጻናትን ሳይቀር በጦርነቱ ላይ አሰማርቷል በማለት የኢትዮጵያ መንግስት በምስል እና በድምጽ ማስረጃ ወንጅሎታል፡፡[36] ይህ የህውሐት ተግባር በክፍል አንድ ያየናቸውን በአለም አቀፍ እንዲሁም በሃገር አቀፍ ደረጃ ተደንግገው የሚገኙ የሰብአዊነት ህጎችን እንዲሁም የሰብአዊ መብት ህጎችን የሚጻረር እና በአለም አቀፍ ወንጀል የሚያስጠይቅ የህግ ጥሰት ነው፡፡ ንጹሀንን መግደል የሰዎችን በህይወት የመኖር መብት መጣስ ብቻ ሳይሆን የሰብአዊነት ህጎችን በመጣስ በጦር ወንጀል እንዲሁም በሰብእና ላይ በሚፈጸም ወንጀል የሚያስከስስ እና የሚያስቀጣ ነው፡፡

የህወሀት ቡድን ንጹሃን ላይ ጉዳት ከማድረስ በተጨማሪ በንጹሀን ንብረቶች ላይም ጉዳት አድርሷል፤ ለማድረስ ሞክሯል፡፡ ለአብነት ያህል በባህርዳር አየር መንገድ ላይ የሮኬት ጥቃት ፈጽሟል አልፎ ተርፎም ጎረቤት ሀገር በሆነችው ኤርትራ አስመራ አየር መንገድ ላይ የሮኬት ጥቃት ተደርጓል፡፡[37] ይህ ብቻ አይደለም የንጹሀን ንብረትን እንደ ከለላ በመጠቀም የአክሱም አየር መንገድን ወደ ጉድጓድነት ቀይሮታል፤ የተለያዩ መንገዶችን አፍርሷል እንዲሁም ድልድዮች ላይ ጉዳት አድርሷል፡፡[38] ከዚህ በዘለለ የህወሀት ሀይሎች የመንግስት እንዲሁም የግል የጤና ተቋማትን በመዝረፍ ነዋሪው የህክምና አገልግሎት እንዳያገኝ አድርገውታል፡፡[39] ይህም በአለም አቀፉ የህግ ድንጋጌ መሰረት በንጹሃን ንብረቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ከመሆን ባለፈ የሰዎችን የህክምና አገልግሎት የማግኘት መብትን መጣስ ነው፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ያለውን የ COVID-19 ስርጭትና የጤና ተቋማት አለመኖር ሊያመጣ የሚችለው ጉዳት ከግምት ውስጥ የሚገባ እና ወደፊት የሚመለከታቸው አካላት በጥናት ሊያረጋግጡት የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በህውሀት ቡድን የተፈጸሙ የሙብት ጥሰቶች በዚህ ብቻ አላበቃም ቡድኑ የስልክ እንዲሁም የሙብራት መስመሮችን በማቋረጥ[40] ሰዎች ሊገናኙ የሚችሉባቸውን መንገዶችን በመዝጋት መረጃ የማግኘት መብታቸውን ጥሷል፡፡ የንጹሃን የመረጃ የማግኘት መብት መጣስ ማለት በአንድም በሌላም መልኩ ሰዎች ስለሚኖሩበት አካባቢ

---

[35] James Butty, Carol Guenablur, 'Ethiopian Human Rights commission alleges atrocities massacre in Tigray', November 25, 2020, 05: 34 pm, https://www.voanews.com/africa/ethiopian-rights-commission-alleges-atrocious-massacre-tigray accessed March 20, 2021.
Ethiopian Human Rights Commission,' country report on human rights practice for 2020,https://www.state.gov/reports/2020-country-reports-on-human-rights-practices/ethiopia/ accessed on June 12, 2021.

[36] Berhak multimedia news, 'Ethiopia accuses TPLF using teen soldiers 'November 10, 2021, https://newbusinessethiopia.com/politics/ethiopia-accuses-tplf-for-using-teenage-soldiers/ accessed April 2, 2021.

[37] Supra note 1

[38] Petter mwai, Christopher Giller, 'Tigray crisis: how the ethiopian army and TPLF clashed over an airport ', November 26, 2020, https://www.bbc.com/news/world-africa-55058212 accessed April 2,2020.
Aljezezra 'Ethiopia accuses tigray forces for destroying Axum airport ', November 23 2020, https://www.aljazeera.com/news/2020/11/23/ethiopia-accuses-tigrayan-forces-of-destroying-axum-airport >accessed April 2 2021.

[39] Supra note 1

[40] Ibid

እንዳያውቁ በማገድ ወደ አደጋ እንዲያመሩ ብሎም የባንክ ግልጋሎት ለመስጠት ባለመቻሉና ገንዘብ የሚያገኙበት ሁኔታ ላይ እክል በመፍጠር መሰረታዊ ፍላጎታቸውን እንዳያሟሉ እንቅፋት መሆን ማለት ነው፡፡ የስልክ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት በተለይም በጦርነት ወቅት ዋና ግልጋሎቱ ንጹሃን እርዳታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እና ከጦርነት ቀጠና ለማሸሽ ነው፡፡ ተዋጊ ወገኖች የድህረ-መረብ ወይም የስልክ መስመርን ማቋረጥን የጠላት ወገን መረጃ እንዳይቀባበል በማገድ እንደ ማዳከሚያ የጦር ስልት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ይህ ሲሆን ግን የንጹሃን ዜጎችን መብት በሚጥስ እና በሚጻረር መልኩ መሆን የለበትም፡፡ የተመጣጣኝነት መርህን ያከበረና ወታደራዊ ጠቀሜታው ከንጹሃን ጥቃት የበለጠ መሆን አለበት፡፡

ወደ ፌደራል መንግስቱ ስንመለስ አንዳንድ ሪፖርቶች በፌደራል መንግስት አካላት የተለያዩ የመብት ጥሰቶች መፈጸማቸውን አትተዋል፡፡ በጦርነቱ ወቅት በፌደራሉ መንግሰት በኩል ንጹሀንን ለመጠበቅ የተወሰዱ እርምጃዎች ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶች አሉ፡፡ ለአብነት ያህል የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በመንግስት ሚድያዎች በመቅረብ የኢትዮጵያ መንግስት የትግራይ ክልል ዋና ከተማ በሆነችው በመቀሌ ከተማ ላይ የአየር ጥቃት ስለሚፈጽም ለዜጎች ራሳችሁን አድኑ የሚመስል አይነት መልእክት አስተላልፈዋል፡፡[41] አለም አቀፉ የጦርነት ህግ ጦርነቶች ከተሞች ላይ እንዳይፈጸሙ አይከለክልም፡፡ ነገር ግን ተዋጊ ወገኖች የተመጣጣኝነት መርህን፣ የመለየት መርህን እንዲሁም ንጹሃን ዜጎች እንዳይጎዱ ቅድመ ጥንቃቄ የማድረግ መርህን እንዲያከብሩ ያስገድዳል፡፡ ይህ የኮረኔሉ መልእክት ንጹሃን ዜጎች እንዳይጎዱ በማሰብ ራሳቸውን እንዲያሸሹ የተሰጠ ይመስላል፤ ነገር ግን ይህ ማስጠንቀቂያ ተደራሽነት ያለው እና ውጤታማ ነው ወይ የሚለው ጉዳይ አሁንም አከራካሪ ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድመን ማስጠንቀቂያው ጊዜውን ጠብቆ ተሰጥቷል ወይ? ንጹሀን አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ ምን ያህል ጊዜ ተሰጣቸው? ንጹሀን በተሰጣቸው ጊዜ አካባቢውን ለቀው መውጣት ይችላሉ ወይ? የሚለውን ማየት ይኖርብናል፡፡ እንደሚታወቀው ጦርነቱ ተጀመረ በተባለበት ወቅት የኤሌክትሪክ እንዲሁም የስልክ መስመሮች ተቋርጠዋል፡፡[42] ይህም ንጹሃን እንኳንስ ከሌላው የሀገሪቱ ክፍል ይቅር እና እርስ በእርስ እንኳን ለመገናኘት የማይችሉበት ከባድ ሁኔታ የፈጠረ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ የመከላከያ ሰራዊቱ በቴሌቪዥን ጣቢያ ቀርቦ ይህንን መልእክት ማስተላለፉ እውነት ለከተማው ነዋሪ ተደራሽ እንዲሆን ነው ወይ የሚለውን አጠያያቂ ያደርገዋል፡፡ እውነታውን ስንመለከት ዜጎች ይህንን ሊሰሙበት የሚችሉበት ምንም መንገድ የለም ስለዚህም ራሳቸውን ከአየር ድብደባ ሊያሸሹበት የሚችሉበት ምንም ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡ እንደ አንዳንድ ጸሀፊያን ገለጻ የአየር ድብደባው አሁን በውል ይሄን ያህል ነው ለማለት በማያስችል ሁኔታ የንጹሃንን ህይወት ቀጥፏል የንጹሃን ንብረቶችንም አውድሟል፡፡[43]ከዚህ በዘለለ የመከላከያ ሰራዊቱ ሞርታር እና ታንክ በመጠቀም የ 47,000 ኢትዮጵያውያን መኖርያ የሆነችውን የሽሬ ከተማ ላይ ጥቃት በመፈጸም 10 ንጹሃንን እንደገደለ Human Rights Watch በሪፖርቱ አሳውቋል፡፡[44] ከዚህ በተጨማሪ BBC News

[41] Ibid

[42] Supa note 1

[43] Betelhem Feleke, Zomiro Rahim, 'several injured in air strickes on tigray capital ', November 19 , 2020, https://www.kctv5.com/several-injured-in-airstrikes-on-tigray-capital-humanitarian-source-says/article_628b7b85-009b-5773-a0ff-7b35e0d6c443.html accessed April 1,2021

[44] Human Rights Watch, 'Ethiopia: unlawful shelling of tigray urban areas 'Feburary 11, 2021, 12 :00 am, https://www.hrw.org/news/2021/02/11/ethiopia-unlawful-shelling-tigray-urban-areas accessed March 10, 2021.

እንደዘገበው MSF የተባለው ድርጅት ሰራተኞች 4 ንጹሃን ዜጎች በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ሲገደሉ የአይን እማኝ እንደሆኑ አስነብቧል፡፡[45]

ዜጎች ማስጠንቀቂያ ደርሷቸው እንኳን በፍርሃት፣ በጤና እክል፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ መሰል ምክንያት አካባቢቸውን ላይለቁ ይችላሉ፡፡ መንግስት እነዚህን ሰዎች በግዴታ ሊያስወጣቸው ወይም ጥበቃ ሊያሳጣቸው አይችልም ይህም ከሆነ እንደማፈናቀል ይቆጠራል፡፡ መንግስት የዜጎችን መብት የማክበር፣ ከጉዳት የመጠበቅ እንዲሁም አስፈላጊ ሁኔታዎችን የማሟላት ግዴታ አለበት፡፡ የመከላከያ ሰራዊቱ የትግራይ ክልል ዋና ከተማ እና የንጹኃን መኖሪያ የሆነችውን መቀሌን ጨምሮ ሌሎች የትግራይ ከተሞችን ተቆጣጥሬአለው ባለበት ሁኔታ እንኳን በንጹሃን ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆኑ የመብት ጥሰቶች ሲፈፀሙ ነበር ይህም መንግስት ዜጎችን የመጠበቅ ወይም ከጉዳት የመታደግ ግዴታውን በአግባቡ ተወቷል ወይ የሚለውን አጠያያቂ ያደርገዋል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በኢትዮጵያ መንግስት መከላከያ ሰራዊት እንዲሁም በህወሀት ቡድን በኩል በንጹሃን ላይ የተለያዩ የመብት ጥሰቶች ሲፈጸሙ ቆይተዋል፡፡ የንጹሃኑ መንገላታት እና ስቃይ በሁለቱ ወገኖች ድርጊት ብቻ አላበቃም ምንም እንኳን በፌደራል መንግስት በኩል የኤርትራ ወታደሮች ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው ጦርነቱ ላይ መሳተፋቸው ዘግይቶ የታመነ ቢሆንም የኤርትራ ወታደሮችም በአስከፊ መልኩ በንጹሃን ላይ ስቃይ እና በደል ሲፈጽሙ ነበር፡፡ ሪፖርቶቹ እንደሚጠቁሙት የኤርትራ ወታደሮች የንጹሃንን ንብረት ዘርፈዋል፣ ንጹሀንን ገለዋል እንዲሁም የተለያዩ ጾታዊ ጥቃቶችን ፈጽመዋል፡፡ ለአብነት ያህል በአክሱም አካባቢ በመቶዎች የሚቆጠሩ ንጹሃን በቤት ለቤት ዳሰሳ ሳይቀር በግፍ ተገለዋል፡፡[46] ከዚህ በዘለለ ከ300 በላይ የሚሆኑ የአስገድዶ መድፈር ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን ከተጠቂዎቹ የተገኘ ምላሽም የኤርትራ ወታደሮችን እንደሚጠቁም ብዙዎች አትተዋል፡፡[47]

ከላይ የተገለጹት ጉዳዮች እንዳሉ ሆነው በማን እንደተፈጸሙ በውል ያልታወቁ ነገርግን የአለም አቀፉን የሰብአዊነት ህግ በመጣስ የተፈጸሙ ጥሰቶችን እናያለን፡፡ በአለም አቀፉ የሰብአዊነት ህግ መሰረት ታሪካዊ መዘክሮች፣ የሃይማኖት ተቋማት እንዲሁም የጤና ተቋማት የጦር ኢላማ መሆን እንደሌለባቸው በክፍል አንድ ማየታችን ይታወሳል፡፡ ነገር ግን ይህን አለም አቀፍ ህግ በመጣስ እከሌ ሃላፊነት ይውሰድ ማለት በማይቻልበት ሁኔታ የተለያዩ የእምነት እና የጤና ተቋማት እንዲሁም ታሪካዊ ቦታዎች ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ ለአብነት ያህል የአልነጃሽ መስጅድ፣ የአማኑኤል ቤተክርስቲያን እንዲሁም የተለያዩ የጤና ተቋማት ላይ ጉዳት መድረሱን ሪፖርቶች ዘግበዋል፡፡[48]

---

[45] BBC, 'Ethiopia's Tigray conflict: MSF witnessed soliders killing civilians', March 25, 2021, < https://www.bbc.com/news/world-africa-56524991> accessed March 10, 2021.

[46] Amnesty International, 'Ethiopia: Eritrea troop massacre of hundreds of Axum civilians may amount to crime against humanity', Feburary 26 2021. https://www.amnesty.org/en/latest/news/2021/02/ethiopia-eritrean-troops-massacre-of-hundreds-of-axum-civilians-may-amount-to-crime-against-humanity/
Addis standard ,' Attorney general admits Eritrean troops executed civilians in axum', May 22,2021,< https://addisstandard.com/news-fed-attorney-general-admits-eritrean-troops-executed-civilians-in-axum-says-53-ethiopian-soldiers-on-trial-for-rape-four-convicted > accessed June 2,2021

[47] New York Times, 'they told us not to resist: sexual violence pervades Ethiopia's war', https://www.nytimes.com/2021/04/01/world/africa/ethiopia-tigray-sexual-assault.html > accessed June 2, 2021.

[48] BBC, 'tigray crisis : Ethiopia to repair Al Nejashi ', 5 January, 2021 <https://www.bbc.com/news/world-africa-55530355#:~:text=The%20Ethiopian%20government

## ልዩ ጥበቃ በተሰጣቸው ሰዎች ላይ የተፈጸሙ የሙብት ጥሰቶች

ልዩ ጥበቃ የተሰጣቸው ሰዎች በጄኔቫ ኮንቬንሽን 3 እና 4 እንዲሁም ተጨማሪ 1 እና 2 ፕሮቶኮሎች ላይ የተቀመጡት ሴቶች፣ ህጻናት እና ስደተኞች ናቸው:: ኢትዮጵያ ከጦርነቱ በፊት ከ100,000 በላይ ለሚሆኑ ኤርትራውያን ስደተኞች መጠለያ ነበረች::[49] ነገር ግን በጦርነቱ ሳብያ ህጻጽ እና ሽመልባ የተባሉ የስደተኛ ካምፖች ጉዳት ደርሰባቸዋል::[50] ስደተኞች ከአንድ ሀገር በፖለቲካ፣ በጦርነት፣ በችግር ወይም በሌላ ምክንያት ሊወጡ ወይም ሊሰደዱ ይችላሉ::እንደ ስደተኛ የተቀበለቻቸው ሀገርም ወደመጡበት ተመልሰው አላግባብ መንገላታት እንዳይደርስባቸው የመጠበቅ ሀላፊነት (principle of non-refoulement)ን የማክበር ግዴታ አለባት:: የኢትዮጵያን ሁኔታ ስናጤን ግን የኤርትራ ስደተኞች ሸሽተው የመጡትን የኤርትራን ሰራዊት ከተጠጉበት በማምጣት አላግባብ እንዲንገላቱና ጉዳት እንዲደርስባቸው በር ከፍታለች::

በትግራይ ክልል የመንገድ አገልገሎት አለመኖር እንዲሁም እንደ አንዳንድ ሪፖርቶች ገለጻ በኤርትራ ወታደሮች ክልከላ ምክንያት ስደተኞች ለምግብ እጦት እንዲጋለጡ እና ሰብአዊ እርዳታ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል::[51] የሰብአዊ ድጋፍ የሚሰጡ ሰዎችም እንግልት ደርሰባቸዋል ከስደተኞች እኩል ተቸግረዋል:: አንዳንድ ሪፖርቶች እንደሚያሳዩት በጦርነቱ 222,000 የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ተፈናቅለዋል 50,000 የሚሆኑት ደግሞ ወደ ሱዳን ተሰደዋል ::[52] ጦርነቱ በሴቶች እና ህጻናት ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል ሴቶች በቡድን ሳይቀር ተደፍረዋል፣ ነፍሰ ጡር እንዲሁም ለወሊድ የደረሱ ሴቶች ህክምና የሚያገኙበት አግባብ ባለመኖሩ ለእንግልት እንዲሁም ለህይወት መጥፋት ተጋልጠዋል::[53] ከዚህ በዘለለ በ Save the Children ሪፖርት መሰረት 5 ሺህ የሚጠጉ ህጻናት ከወላጆቻቸው ጋር ተነጣጥለዋል እንዲሁም ወላጆቻቸውን በሞት አተዋል::[54] ከወላጆቻቸው ጋር የተነጠሉ ህጻናት በስደተኛና ጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ለረሃብ፣ ለአካላዊ እና ጾታዊ ጥቃቶች ተጋላጭነታቸው የጎላ ነው:: በአጠቃላይ በአለም አቀፍ ደረጃ ተጋላጭ እንደሆኑ ታምኖበት ልዩ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ ሰዎች መብት በጦርነቱ ወቅት በእጅጉ ተጥሷል፣ ህይወታቸውን አተዋል በአካላቸው ላይ ጉዳት ደርሷል::

## ማጠቃለያ

በመጀመሪያው የዚህ ጽሁፍ ክፍል ለማየት እንደተሞከረው ንጹሃን በጦርነት ወቅት በአለም አቀፍ የሰብአዊነት ህግ እንዲሁም በአለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ህግ መሰረት የተዋጊ ወገኖችን ግዴታ እና የንጹሀንን መብት

%20has%20promised,of%20Islamic%20figures%20were%20damaged.> , accessed February 2, 2021

49 Supra note 1

50 Wion, 'Refugee group condemns damage at camps hit by Tigray war', February 08, 2021, <https://www.wionews.com/world/refugee-group-condemns-damage-at-camps-hit-by-tigray-war-362236 > accessed February 20, 2021.
UNHCR, 'UNHCR finds dire need in Eritrean refugees' camp cut off in tigray conflict', January 19 2021, <https://www.unhcr.org/news/briefing/2021/1/6006a31a4/unhcr-finds-dire-need-eritrean-refugee-camps-cut-tigray-conflict.html> accessed February 5 2021.

51 Ibid

52 Ibid

53 Supra note 1


54 Save the children 'six month on: almost 5,000 children separated from parents by conflict in Tigray' May 4, 2021, <https://www.savethechildren.net/news/six-months-almost-5000-children-separated-parents-conflict-tigray#:~:text=May%202021%20%2D%20Ethiopia-,Six%20months%20on%3A%20Almost%205%2C000%20children%20separated,parents%20by%20conflict%20in%20Tigray&text=Thousands%20of%20children%20are%20currently,according%20to%20Save%20the%20Children> accessed June 1, 2021.


ኢትዮጵያ አባል ከሆነችባቸው አለም አቀፋዊ ህጎችና ከሀገራችን የህግ ማእቀፎች ጋር በማመሳከር አይተናል፡፡


በክፍል ሁለት የህጉ ማዕቀፍ እንዳለ ሆኖ  በልዩ ሁኔታ በትግራይ ክልል ባለው ጦርነት ላይ ንጹሃን እንዲሁም ልዩ ጥበቃ ያላቸው ሰዎችን የሙብት መከበር ስናጤን ፍጹም ተቃራኒ በሆነ መልኩ ከፍተኛ የሆኑ የሙብት ጥሰቶች በተለያዩ አካላት  ሲፈጸሙ እንደቆዩ አይተናል፡፡ አንዳንድ የምስል እና የድምጽ ዘገባዎች እንደሚያስረዱት ንጹሀን ለከፋ እንግልትና ስቃይ በመከላከያ ሰራዊት፣ በህውሀት ቡድን እንዲሁም በኤርትራ ወታደሮች ተጋልጠዋል ሙብታቸውም ተጥሷል፡፡ አሁንም ቢሆን በትግራይ ክልል የሚገኙ ዜጎች ፣ ስደተኞች እንዲሁም የእርዳታ ሰራተኞች በዛም አነሰ ለተለያዩ የሰብአዊ ሙብት ጥሰቶች ተጋላጭ ናቸው፡፡ አንዳንድ ዘገባዎች የክልሉን ነዋሪ ዋቢ አድረገው እንደሚገልጹት የኤርትራ ወታደሮች በንጹሃን ላይ  ዘርፈ ብዙ ጉዳት ያደረሱ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ከሀገሪቱ ሉዐላዊነት ጋር የሚጻረር እና በአፋጣኝ መፍትሄ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ በትግራይ ጦርነት ወቅት መንግስት ሀላፊነቱን አልተወጣም በሚያስብል ደረጃ ከፍተኛ የሙብት ጥሶቶች ተፈጽመዋል፡፡ ለወደፊት መንግስት ይህንን የንጹሀንን ስጋት እና ጥቃት ከግምት ውስጥ በማስገባት ሀላፊነቱን ሊወጣ እና ህግን ሊያስከብር እንዲሁም ጥፋተኛ የህውሀት አባላትን ለህግ በማቅረብ ዘላቂ ሰላም የመፍጠር ግዴታውን ቢወጣ እና እየደረሱ ላሉ የሰብአዊ ሙብት ጥሰቶች እልባት ቢሰጥ  መልካም ነው፡፡

ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጲያ በሶስት ርእሶች ላይ ጥናታዊ ጽሁፎችን በማጠናቀቅ ሰኔ 10/2013 ዓ.ም በይፋ አስመርቋል።



# Association for Human Rights in Ethiopia

AHRE

ስብስብ ለሰብአዊ መብቶች በኢትዮጲያ